የሚያያቸው መሆኑን ለፍ/ቤቱ ያስረዳውም ከዚህ በመነሣት እንደሆነ መገመቱ የሚያስቸግር አይደለም፡፡ በበኩላችን እንደምናየው የአመልካች እና የተጠሪ አብሮ የመኖር ሁኔታ በፌዴራሉ መንግሥት የቤተሰብ ሕግም ሆነ በአማራ ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ሕግ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብኖ መኖርን በተመለከተ የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚገባ የሚያሟላ ነው፡፡ ሲጠቃለል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የጋብቻ ግንኙነት አለ ለማለት ባይቻለም፤ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው መኖራቸው ግን የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ በመሆኑም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የሚያሣይ ሁኔታ በሚል በስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ትክክል አይደለም፡፡ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 09277 ሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደባልና ሚስት ሆነው አብረው ኖረዋል ብለን ወስነናል፡፡ ይህ በንብረት ግንኙነታቸው በኩል የሚኖረው ውጤት በክልሉ ሕግ ጉዳዩ በተጀመረበት ወረዳ ፍ/ቤት ቀጥሎ ይታይ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33411

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድኀን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አለቃ ኪሮስ ገብሩ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአፈፃፃም ክርክር ሲሆን፣ በዋናው ጉዳይ ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን በስምምነት ለማፍረስ ተዋውለው ስምምነታቸውን በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. በት/ብ/ክ/መ/ ሕንጣሎ ዋጅራት ወረዳ ጣቢያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት በውሣኔ እንዲያፀድቀው አድርገዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች ተጠሪው በስምምነቱ መሠረት የጋራ ንብረት ክፍፍሉን ሊፈጽሙ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል በሚያዝያ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. በት/ብ/ክ/መ/ ኢንጣሎ ወረዳ ጣቢያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት የጋራ ያሏቸውን ንብረቶች በመዘርዘር ያካፍሉኝ ሲሉ በተጠሪው ላይ የአፈፃፀም ክስ መሥርተዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ /የሥር የአፈፃፀም ተከሣሽ/ በሚያዝያ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ የአሁን አመልካች በክሣቸው የዘረዘሯቸውን የጋራ ንብረቶች ለማካፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀው በክሱ ከተዘረዘሩት ንብረቶች መካከል የወፍጮ ድርጅት ያካፍለኝ ለተባለው ፀጋዬ ገብሩ ከተባሉት ግለሰብ በ10,000 ብር የገዛነው ቢሆንም ስመ ንብረቱ ያልተዛወረ የግዢ ውሉም ያልፀድቀ በመሆኑ ሳካፍላት አልችልም ስለዚህ ወይ ባለቤትነት ስም እስኪዛወር ትጠብቅ ወይ የግዢ ገንዘቡን ግማሽ ብር 5000 (አምስት ሺህ) ትውሰድ ሲሉ ተከራክረዋል።

የአፈፃፀም ክርክሩ የቀረ 255 ነያ ደጀን ማ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ጉዳት መርምሮ በግንቦት 11 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ፣ ቀደም ሲል ቀርቦ በፀደቀው የፍቺ ስምምነት መሠረት በጣብያ ደጀን ዓዲኾሎ የሚገኘው የወፍጮ ድርጅት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት መሆኑ መግልጽ የሠፈረ እና ይህንኑ ድርጅት እኩል ለመካፈል የተስማሙ በመሆኑ ግራ ቀኙ የወፍጮ ድርጅቱን ከነ ሙሉ መሣሪያዎቹ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል።

የጣብያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኙት የአሁን ተጠሪ ቅሬታቸውን ለህንጣሎ ወረዳ ፍ/ቤት በይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል። በመቀጠል ተጠሪ ቅሬታቸውን ለት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል።

የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ አመልካችን በማስቀረብ ግራ ቀኙን ያከራከረ ሲሆን በነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የክርክሩ መነሻ የሆነው መፍጮ በአሁን ተጠሪ ወንድም በአቶ ፀጋዬ ገብሩ ስም እንደሚታወቅ የአሁን አመልካች አልካዱም። ንብረትነቱ በአሁን ተጠሪ ስም እንደተላለፈም የቀረበ ማስረጃ የለም፣ በመሆኑም ለዚህ ወፍጮ ግዢ ገንዘብ እንደተከፈለ እንጂ ውል ተፈጽሞ ወደ ስማቸው እንደተላለፈ እስካልተደረጋገጠ የጋራ ተብሎ ወደ ተከራካሪዎቹ የትዳር ንብረት ክፍፍል ሊገባ አይችልም በሚል ግራ ቀኙ ለወፍጮ ግዢ የተከፈለውን ብር 10,000 የጋራ በመሆኑ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉት ሲል የስር ፍ/ቤችን ውሣኔ ሽሯል።

ይህ መዝገብ ለዚህ ችሎት የቀረበውም የት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪው ለአመልካች ወፍጮ የተገዛበትን ዋጋ ብር 10,000 ያካፈሏቸው ሲል የሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች በጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መሠረት ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ሲጠቃለል በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. ባደረግነውና በፍ/ቤት በፀደቀው የፍቺ ስምምነት የወፍጮ ድርጅቱን እኩል ለመካፈል በግልጽ ተስማምተን፣ የስሙ አለመዛወር የንብረት ክፍፍሉን ተግባ 256 ሚያግድ ሆኖ ሣለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ከተከራካሪዎች ባልቀረቡለት ጥያቄ የግዢ ውሉ እንደሚፈርስ አድርጎ ለግዢ የተከፈለውን ገንዘብ እንድንካፈል መወሰኑ አላግባብ በመሆኑ ይሻር የሚል ነው።

ይህም ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ የክርክሩ ምክንያት የሆነው ወፍጮ ድርጅት ባልና ሚስቱ /አመልካችና ተጠሪ/ ቢገዙትም በስማቸው አልዞረም በሚል የጋራ ሀብት አይደለም ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል። እኛም የግራ ቀኙን ክርክርና የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች መርምረናል። እንደመረመርነውም ተጋቢዎቹ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን የወፍጮ ድርጅት በተመለከተ በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. ተደርጎ በፍ/ቤት በፀደቀው የፍቺ ስምምነታቸው ላይ ክፍፍሉን አስመልክቶ በግልጽ ፈቃዳቸውን ሰጥተው ተስማምተዋል። ይህን ስምምነት ግራ ቀኙ ያልካዱት በሌላ ስምምነት ያልቀየሩት ወይም ያላሻሻሉት እና በፍ/ቤትም የፀደቀ ከመሆኑ አንፃር ይህ ስምምነት በግራ ቀኙ መልካም ፈቃድ እስካልተሻረ ድረስ ተጋቢዎቹ በስምምነቱ ቃል የማይገደዱበት ምክንያት አይኖርም። በሌላ በኩል በማንኛውም የክርክር ደረጃ ቀርቦ በአከራካሪው ንብረት ላይ መብት አለኝ፤ የጋራ ሀብት ተብሎ ለግራ ቀኙ ሊካፈል አይገባም በሚል በ3ኛ ወገን የቀረበ ክርክር የለም። ተጠሪው